የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር
Ref. No. መአ/3/22/203
ቀን
Date 24/04/203

# ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## የመድብለ ፓርቲን ሥርዓት ጨፍልቆ ኢህአዴግ የማያቋቁመው መንግሥት የአምባገነንነት መገለጫ ነው!

ኢህአዴግ የደርግን መንግሥት በጠብመንጃ ከሥልጣን አስወግዶ ራሱን በኃይል መንግሥት ካደረገ በኂላ በየ5 ዓመቱ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ አከናውናለሁ ቢልም በየወቅቱ ያደረጋቸው ምርጫዎች ዓለም አቀፍ የምርጫ መስፈርትን ያላሟሉና በየዙሩ ምርጫውን በማጭበርበር የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ ሳያገኝ በጉልበት ወደ ሥልጣን መምጣትን የተለመደ ባሕሪው አድርጎ ቀጥሎበታል፡፡

በ1987 ዓ.ም እና በ1992 ዓ.ም የተደረጉ ምርጫዎችን ስንመለከት ተቃዋሚዎች በየክልሉ ገብተው በምርጫው እንዳይወዳደሩ የተለያዩ መሰናክሎችን በመፍጠርና ሕዝብ በፈለገው የፖለቲካ ፓርቲ ተደራጅቶ የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ የመምረጥ ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን በማፈን ራሱን ከአጋሮቹ ጋር እያወዳደረ የኢህአዴግን አሸናፊነት በኃይል እያወጀ መጥቷል፡፡

በ1997 ዓ.ም ደግሞ በመላ ሀገሪቱ ያሸነፈውና መንግሥት ለመመስረት አብላጫ መቀመጫ ያገኘውን ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን በኃይል በመንጠቅ የፓርቲውን አመራሮችና አባላት በማሰር ለ3ኛ ጊዜ ኢህአዴግ የራሱን መንግሥትነት በኃይል መመስረቱ ዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ የመሰከረው ሐቅ ነው፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

በ2002 ዓ.ም በተደረገው ምርጫም የተከናወነው የተለየ ነገር አልነበረም፡፡ ገዢው ፓርቲ እንደሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምርጫው ውስጥ ገብቶ የተወዳደረ ቢሆንም የፈረመውን የምርጫ ሥነ-ምግባር ሕግ፣ የምርጫ ሕግና ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ የምርጫውን ሜዳ ነጻና ፍትሐዊ ሳያደርግ መራጩን ሕዝብ በማስፈራራት፣ በማዋከብ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ዕጩ ተወዳዳሪና የምርጫ ታዛቢዎችን በማሰርና በማንገላታት የራሱን አባሎች የምርጫ አስፈጻሚ በማድረግ የፓርላማና የክልል መቀመጫን ሙሉ በሙሉ አሸንፌአለሁ በማለት ለ4ኛ ዙር ራሱን በጉልበት ለመንግሥትነት አብቅቷል፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የ2002 ዓ.ምን ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ ሂደትና ውጤት የማይቀበለውና ምርጫው እንዲደገም ቢጠይቅም ገዢው ፓርቲ “የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ” በማለት የአንድን ፓርቲ የበላይነት በማወጅ ራሱን ለ4ኛ ዙር ወደ መንግሥትነት ለውጧል፡፡ ኢህአዴግ የሀገሪቱን የመገናኛ ብዙሐን በቁጥጥሩ ሥር አውሎ የራሱ ፕሮፓጋንዳ ማሰራጫ በማድረግ፣ የሀገርና የሕዝብ ሀብትና ንብረትን ለምርጫ በመጠቀም፣ የውጭ ሚዲያዎችን ነጻ መረጃ ለሕዝብ እንዳይሰጡ በማፈን የተደረገ ምርጫ በየትኛውም መስፈርት ነጻና ፍትሐዊ ሊባል እንደማይገባ መኢአድ እና ትክክለኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአጽንኦት ያረጋግጣሉ፡፡ የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድንም ምርጫው የዓለም አቀፍ የምርጫ መስፈርትን እንደማያሟላ በመጀመሪያ ዙር መግለጫው ዘግቧል፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መኢአድም ምርጫው ሳምንታት ሲቀሩት እየደረሱ ያሉት የሰብአዊ መብት ጥሰትና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዶችን  አስመልክቶ በአስቸኳይ እንዲስተካከሉ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የጻፈው ደብዳቤ፣ የምርጫውንም ውጤት አስመልክቶ በየክልሉ የታዩ ችግሮችና የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ያደረጉትን የምርጫ ማጭበርበር ለኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንና ለራሱ ለገዢው ፓርቲ ኢህአዴግም በላክነው ጥራዞችና በሰጠነው ጋዜጣዊ መግለጫ የምርጫውን ውጤት እንደማንቀበለው አስታውቀናል፡፡



ይሁን እንጂ ገዢው ፓርቲ የተፈጠሩትን ችግሮች ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ለመነጋገርና ለመደራደር ሳይሞክር ራሱን አሸናፊ በማድረግ መንግሥት መመስረቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ የዘመናት የዲሞክራሲ ጥያቄ ማፈን ስለሆነ የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንና የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ እውቅና እንዳይሰጡ መኢአድ እየጠየቀ የኢትዮጵያ ሕዝብና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ለሰላማዊ ትግሉ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እንዲነሱ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ጌታቸው ባያፈርስ
የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ